# "ጉዱ...ጉዴ"!!

**አየነው አሰፋ**

07/18/14

"ጉዱ...ጉዴ" የሚል የክራር ዘፈን አለው አሜሪካን የሚገኘው ኮሜዲያን መስከረም፡፡ ጉዱ...ጉዴ እድምተኛውን ከልብ ፈንቅሎና ኮርኩሮ ያሳቀና ያንከተከተ ነው፡፡ የዘንድሮው ጉዱ...ጉዴ እዚያው አሜሪካን የሚዘፈንለት ለግንቦት ሰባት እና ለኢሣት ሣተላይት ቴሌቪዥን መሆኑ ነው፡፡ የግንቦት ሰባት "ማስተር ማይንድ" ያለጥርጥር  አንዳርጋቸው ፅጌ ነው፡፡ ብርሃኑ ነጋ በኢሕአፖ ጊዜ ሱዳን ቀጥሎም አሜሪካን ገብቶ ኖሮ ተማረና ዶክተር ሆነ፡፡ አንዳርጋቸው ፅጌ ደግሞ ከኢሕአፖ፣ ከኢሕዴን በኋላም እስከ ኢሕአዴግ ብአዴን ድረስ በትግል ውስጥ ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን በሽግግር መንግሥት ወቅት በአዲስ አበባ መስተዳደር በኢሕአዴግ አመራር ውስጥ ሦስተኛው ቁልፍ ሰው ነበር፡፡

የዛሬን አያድርገውና አሁን በሥልጣን ላይ ላሉት ቀደምቶችም የቅርብ ጓደኛ ነበር፡፡ በአመለካከትና በመስመር መለያየት ጥንትም የነበረ፣ ያለና የሚኖር በመሆኑ ይህ መከሰቱ አያስገርምም፡፡ የአንድ ዘመን ወዳጆች በሌላ ወቅት በጎሪጥ የሚተያዩበት አጋጣሚ አለና፡፡ የ1997ቱን የቀለም አብዮት በኢትዮጵያ ለመምራት አንዳርጋቸው ፅጌ ከእንግሊዝ ክፍሉ ታደሰ ከአሜሪካን ወደ አዲስ አበባ የገቡት ቀደም ብለው ከሁለት ዓመት በፊት ነበር፡፡

በወቅቱ የቅድሚያ ትኩረታቸው የግል ሚዲያ ማቋቋም ሆነ፡፡ በክፍሉ ታደሰ የሚመራው አዲስ ዜና የግል ጋዜጣና አንድ ሌላ መፅሔት ተቋቁመው ሥራ ሲጀምሩ የኩባንያው ባለቤቶች እነ ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል፣ እነ ዶክተር ብርሃኑ ነጋ፣ እነ አቶ አበበ ወርቁና ሌሎችም ነበሩ፡፡ የግል ኤፍ.ኤም ራዲዮ ጣቢያ ለማቋቋም የተለያዩ መሣሪያዎችን  ከውጭ አገር አስገብተው ሰልጣኞችንም ወደ ውጪ አገር ልከው ነበር፡፡

አዲስ ዜና ጋዜጣ ከ1997 ዓ.ም በኋላ ጥቂት ተጉዞ ብዙ ሳይገፋ ቀረ፡፡ ሊያቋቁሙት የነበረው የጠየቁት ኤፍ.ኤም ራዲዮ ጣቢያ ሁለት ሚዲያ (ጋዜጣና ራዲዮ) በአንድ ላይ መያዝ አይቻልም በሚለው ሕግ ሳይቻላቸው ቀረ፡፡

በወቅቱ የነበሩት ተቃዋሚ ፖርቲዎች መኢአድ፣ ኤዴፓ፣ ቀስተ ደመናና ሕብረትን የመሳሰሉት ከብዙ የሽምግልና ጥረት በኋላ በአንድ ሆነው ቅንጅትን እንዲመሰርቱ ያደረጉት ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያምና ዶክተር ብርሃኑ ነጋ ነበሩ፡፡ ሕዝብ የማደራጀቱና ለአመፅ የማንቀሳቀሱን አሠራር፣ አደረጃጀትና አወቃቀሩን የመሩት ከጀርባ ያሉትና የረዥም ጊዜ የትግል ተሞክሮና ልምድ የነበራቸው ክፍሉ ታደሰና አንዳርጋቸው ፅጌ ናቸው፡፡

የግሉን ሚዲያ ሙሉ በሙሉ ማለት ይቻላል በገንዘብ እየረዱ ለዓላማቸው አሰልፈውታል፡፡ የሠላማዊ ትግል ሥልት፣ የአመፅ፣ የእምቢታ ስትራቴጂ በሚል በቀጥታ እየታተመ የሚሰራጨው ጥሪ የሚተላለፈው በምኒሊክ፣ አስኳል፣ ሣተናው፣ ኢትኦጵ፣ አባይ፣ ህዳር፣ ነፃነት፣ ልሣነ ሕዝብ፣ ወንጭፍ፣ አዲስ ዜናና ሌሎችም የግል ጋዜጦች ስለነበር በቀላሉ ሕዝቡን ለማግኘትና መልዕክታቸውን ለማድረስ ችለው ነበር፡፡

ዛሬ እነዚህ ጋዜጦች ባይኖሩም ሕልውናቸው መልኩን ቀይሮ ቀጥሏል፡፡ ቀጣዩን የቀለም አብዮት በአዲስ ሥልት ለመምራት የዛሬ ሦስት ዓመት ገደማ ሥርጭታቸውን በስመ የፍቅር መጽሔት ጀምረው ወደ ፖለቲካ መጽሔትነት ቀስ በቀስ በመሸጋገር አጀንዳቸውን ሲያሰርፁ ቆይተዋል፡፡

አሁን በሥራ ላይ ያሉት ተቃዋሚ የፅንፈኛው ልሣን የሆኑት ጋዜጦችና መጽሔቶች በሕግ ተጠያቂነት ሥር ሲውሉ ሌሎች በተለያዩ ግለሰቦች ባለቤትነት የተለያዩ ሥያሜዎች ያላቸው የግል ፕሬሶች ፈቃድ ማውጣት እንዳለባቸው አስቀድመው የወሰኑ ስለሆነ እሥር ቤቶች እስኪሞሉ ድረስ ብንታሰርም እንቀጥላለን እንዳሉት ሁሉ በአዲስ ስምና ፈቃድ እየወጡ ትግሉን ይቀላቀላሉ፡፡ ሕዝቡንም ለአመፅ ገፍቶ እንዲነሳ፣ በድፍረት እንዲሰለፍና እንዲጋፈጥ ይህ ቀረሽ የማይባል ጥረት አድርገዋል፤ ይህም ቢሆን ይታወቃል፡፡

በዚህ መልኩ በጣም ውስን ከሆኑት የግል ጋዜጦች በስተቀር ሌሎቹ መጽሔቶችና ጋዜጦች በሙሉ የፅንፈኛው አክራሪ ተቃዋሚ ልሣኖች ናቸው ብሎ ለመደምደም ይቻላል፡፡ ስለዚህም ነፃና ገለልተኛ፣ ሚዛናዊ የሆነ የግል ፕሬስ በአገሪቱ አለ ብሎ ደፍሮ ለመናገር የማይቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ የፅንፈኛው ተቃዋሚ አንዱ ፖለቲካዊ ሥልት በራሱ ገንዘብ አባላቱና ደጋፊዎቹ ጋዜጣና መጽሔት እንዲከፍቱ አድርጐ የፈለገውን ፕሮፓጋንዳ እንደልቡ እያዛመተና እያሰራጨ የሕግ ተጠያቂነት ሲመጣ መንግሥት የግል ጋዜጦችን አገደ፣ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት ሞቶ ተቀብሯል የሚለውን ፕሮፓጋንዳ ለምዕራቡ ዓለም መንግሥታትና ለጋሽ ድርጅቶች ይነዛሉ፣ የፕሬስ፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋችና ተከራካሪ ነን ለሚሉት ሲፒጄ፣ ሂዩማን ራይትስ ዎችና ለሌሎችም ይህንን ሐሰተኛ መረጃ በማስተላለፍ በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ ጫና እንዲደረግ፣ እርዳታም እናስቆማለን ሲል አክራሪውና ፅንፈኛው የተቃዋሚ ኃይል ያቀደውና የጠነሰሰው ሴራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ሲፒጄና ሂዩማን ራይትስ ዎች መሰሎቻቸውም የኒዮ ሊበራል ኃይሎች ዋነኛ መሣሪያ ሲሆኑ በየአገራቱ የውስጥ ጉዳይ እየገቡ እንዳሻቸው የሚፈተፍቱ፣ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስከብሩ መንግሥታት በየአገሩ ለመመሥረት ካላቸው ብሔራዊ ጥቅምና ፍላጐት አንፃር እንጂ የሚጮሁት እውነትም ለሕዝብ አስበው፣ ተጨንቀውና ተቆርቁረው አይደለም፡፡

ትናንትም ዛሬም ይህን በማቀናጀት በዋና መሐንዲስነት ሲመሩና ሲያቀናብሩ የነበሩት፣ የ97ቱን ያልተሳካና የጨነገፈ የቀለም አብዮት፣ አሁን ደግሞ በ2007 ለሚካሄደው ብሔራዊ ምርጫ ከአራት ዓመታት በፊት ጀምሮ እስከ ዛሬም የሕዝባዊ አመፅን የትግል ስትራቴጂ ቀመር በዝርዝር የነደፉት፣ ለዚህም ተግባር የፍቅር መጽሔቶችን ወደ ፖለቲካ መጽሔትነት በመቀየርና ከፍተኛ ገንዘብ በማፍሰስ አዘጋጆችንም ሪፖርተሮችንም በከፍተኛ ደመወዝ በመቅጠር የቤት ኪራይና የሠራተኛ ደመወዝና ማሣተሚያ ገንዘብ በመሸፈን ለሊት ቀን እንዲሰሩ ያደረጉት የፅንፈኛው ግንቦት ሰባት አመራሮች ናቸው፡፡

ኢሣት ሣተላይት ቴሌቪዥንም የተቋቋመው፣ የሚመራውና የሚተዳደረው በእነሱውና በአባቶቻቸው ነው፡፡ ዋነኛ ግቡም ፀረ መንግሥት የሆኑ፣ ሕዝብን ለአመፅና ተቃውሞ ያነሳሳሉ ብለው የሚያምኑባቸውን የሐሰት ፕሮፓጋንዳዎች

በስፋት ማሰራጨት ነው፡፡ ይህንንም በመቀበል በአገር ውስጥ የእነሱው መጽሔቶችና ጋዜጦች በተለያየ መልኩ እየተቀባበሉ በማሳተም ተሰራጭቶ ሕዝብ ውስጥ እንዲደርስ ያደርጋሉ፡፡ ይህ የከፋ ጥላቻን ሰንቆ በፍፁም ስሜታዊነትና ጅብደኝነት ተሞልቶ አገሪቱን የደም መፋሰስ ማዕከል ለማድረግ እያቅራራና እያናፋ የሚገኘው ፅንፈኛ ኃይል በእሱ ቀመርና ሥሌት አገር ቤት በመለመለውም ኃይል በመደገፍ ድል አገኛለሁ ብሎ ከንቱ ሕልም አልሟል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉን ተረድቶና ተገንዝቦ ቀድሞ እንደሄደ ለመረዳት ያልቻለ፣ ገና ከሰመመኑ ያልነቃ፣ ዳፍንትና ጨለማ ውስጥ ተዘፍቆ የሚዛብር ኃይል ነው፡፡

አገሪቱና ሕዝቧ በምን ደረጃ ላይ እንዳሉ እንኳን በቂ ግንዛቤ የለውም፡፡ ጽንፈኛው ባሕር ማዶ ሆኖ እንዲሁም አገር ቤት ባሉት በከፋ የጎሣ ጥላቻ ተወጥረው የመተላለቅና የምፅዓት ቀንን እየናፈቁ በሚገኙት ከንቱዎች አማካይነት ሕዝብ ከሕዝብ የሚያቀራርብ፣ ችግርን በሠላማዊና በሰለጠነ መንገድ የሚፈታ፣ አብሮነትና ፍቅርን የሚያጉልበት ሳይሆን እርስ በእርስ የሚያባላ፣ የከፋ የዘረኝነት ቅስቀሳን ሲያዛምቱ የኖሩት ደጋፊዎቻቸውና አባላቶቻቸው የሚሰሩት ሥራና እንቅስቃሴያቸው ከሕዝብ የተሰወረ አይደለም፡፡

በዚህ ሴራቸው በቀለም ያልገፉ አዛውንቶችን፣ ጎልማሶችን፣ አሮጊቶችን ሁሉ በየመንደሩና በየእድሩ እያሰባሰቡ፣ ገንዘብም እየሰጡ ጭምር ዘረኛ ቅስቀሳ ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ በቀንና በሌሊት የሚሰሩ የአነስተኛ ታክሲና ሚኒ ባስ ሾፌሮች፣ በሕዝብ መገልገያ ቤቶችና በመዝናኛ ሥፍራዎች፣ በምሽት ክለቦች የሚሰሩ ሠራተኞች፣ በየኮንቴይነሩ ባሉ አነስተኛ ሸቀጥ ነጋዴዎች፣ በአብዛኛው በጡረታ የተገለሉ የሲቪልና የቀድሞ ሠራዊት አባላትን በደጋፊነትና በአባልነት ሙያቸውንም ለመጠቀም በማሰብ እንደያዟቸው ለአስተባባሪዎቹም ክፍያ እንደሚሰጥ ጭምር እነ ግንቦት ሰባት ያልታወቀ መስሏቸው ከሆነ ተሳስተዋል፣ ይህም ቢሆን ይታወቃል፡፡

ከኢሕአዴግ የተባረሩና የተሰናበቱትንም በማቀፍ በጋዜጠኝነት ስምና ሽፋን አደራጅተው ጽሁፎችን በመደበኛነት በየመጽሔቱ በቅብብሎሽ የሚያሰራጩበት፣ ይህንንም የማስተባበር ሥራ እነማን እንደሚከውኑት ይታወቃል፡፡ በጋዜጣና መጽሔት ሥራ አከፋፋይነት ያለሕጋዊ ፈቃድና የመንግሥት ግብር ለዓመታት

የአየር በአየር ሥራ እየሰሩ ሀብት አካብተውና ስንቱን የእነሱን መስመር የማይቀበልና የማይደግፍ፣ በግልና ሚዛናዊ፣ ገለልተኛና ኃላፊነት የሚሰማቸውን የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች በተለያየ ሴራና ወንጀል ከገበያ ውጭ እንዲሆኑ አድርገዋል፡፡ የአገሪቱን የግል ፕሬስ እድገት በመግደል፣ የፕሬሱን ብዝሀነት በማጥፋት እንዴትና እነማን በከፍተኛ ገንዘብ እየተደጎሙ፣ የግሉን ፕሬስ የፅንፈኛና አክራሪ ኃይሎች ልሣንና መፈንጪያ እንዲሆን እንዳደረጉት ይህም በበቂና ከበቂ በላይ በሆነ ማስረጃ ይታወቃል፡፡ ይህን መረብ ተጠቅመው ጥላቻን ሲዘሩ፣ መልካሙን ሥራ ጥላሸት ሲቀቡ፣ የአገሪቱን ልማትና እድገት ሲያጣጥሉ፣ የመሪዎችንና የግለሰቦችን ስብዕና ሲያንቋሽሹና እንዳሻቸው ጭቃ ሲቀቡ፣ አልፈው ተርፈውም በድርጅታዊ ተልዕኳቸው ኢሕአዴግ ተሰነጠቀ፣ ተከፋፈለ፣ እርስ በእርስ ተፋጠጠ ወዘተ...እያሉ የሕዝቡን ሥነ ልቦና ሲያናጉ፣ ሠላምና መረጋጋት እንዳይኖር፣ መተማመን እንዲጠፉ፣ ጥላቻና ጥርጣሬ እንዲሰፍን፣ ምርት እንዲስተጓጎል፣ ይህንን የታቀደ የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ወንጀል እየረጩ ሲነግዱ፣ በእነማን ታቅዶ በየግሉ መጽሔትና ጋዜጣ እንደሚሰራጭ ያልታወቀ ወይንም የማይታወቅ መስሏቸው ከሆነ አሁንም ተሳስተዋል፣ ይህም ቢሆን በሚገባ ይታወቃል፡፡

ከአዲስ አበባ የአስመጪና ላኪ ንግድ ፈቃድ አውጥተው ዱባይና የመን ይመላለሱ የነበሩና እንግሊዝ፣ አሜሪካና ጀርመን የሚመላለሱ ሰዎች እውነት ለንግድ ሥራ ነው ወይንስ ሌላም የተሸፈነ ጉዳይና የሚገናኟቸው የጽንፈኞቹ ሰዎች አሉ? የጽንፈኛው ገንዘብስ ወደ አገር ቤት የሚገባው፣ በባንክ ነው ወይንስ በነጋዴ አስመጪና ላኪነት በሚሰሩ ሰዎች የግል አካውንት? ወይንስ ከውጭ አገር በሸቀጥና እቃ መልክ ወደ ኢትዮጵያ በግለሰቦች አማካይነት ገብቶ ተሸጦ የሚገኘው ገንዘብ ነው ለእኩይ ሥራቸው ወጪ መሸፈኛ የሚያውሉት? ይህም ቢሆን በሚገባ ይታወቃል፡፡ ግንቦት ሰባት በሚሰጠው መመሪያ አንድነት፣ ሰማያዊ ፖርቲና መድረክም ጭምር የተለያዩ ቢሆንም በውስጥ ትስስር ለአመፅ ማስፈፀሚያ ዓላማ የሚላክላቸውን ገንዘብ ሥርዓቱን በሚኮንኑና ሰልፋቸውን ከእነሱ ጋር ባቆራኙ ግለሰብ ነጋዴዎች አማካይነት እንደሚደርሳቸው ይህም ቢሆን ይታወቃል፡፡

ምስጢራዊ ስብሰባዎቻቸውንም በአዲስ አበባና ከአዲስ አበባ ውጭ በሚገኙ ሆቴሎች በተለያየ ሽፋን እንደሚያካሂዱ፤ አልፎ ተርፎም በቤተክርስቲያኖችና መስጊዶች ውስጥ  እንደሚሰበሰቡ ይህም ቢሆን ይታወቃል፡፡ የቀንና የሌሊት ፈረቃን በመጠቀም የመረጃ መሰብሰብ ሥራ በየአካባቢው በመደቧቸውና ተከፋይ በሆኑ ጎረምሶችና ጡንቸኞች አማካይነት እንደሚካሄድ፤ ወጣት ሴቶችን በማቀናጀት ከእይታ ለመከላከል ተሸፍነው እንደሚንቀሳቀሱ ይታወቃል፡፡ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳቸው ሕዝብ ለመዝናናት በብዛት በሚገኝበት ሥፍራዎች ግልፅ የአመፅ ጥሪና ቅስቅሳ እንደሚደረግ፤  የጥላቻና የአመጽ ጥሪ፤ የአትነሳም ወይ ቅስቀሳ ማስተላለፊያ መድረኮች መሆናቸውም ይታወቃል፡፡ ትምህርት ቤቶች፣ ኮሌጆች፣ ዩኒቨርስቲዎች እንዲሁም የተለያዩ ኃይማኖቶች የእምነትና የትምህርት መስጫ መሰብሰቢያ ቦታዎች፤ የሙያና የሲቪክ ማሕበራት አመራርና አባላትንም በማጥመድ በመድረኩ የጥላቻና የአመጽ ሥውራዊ መልዕክት ማስተላለፊያ ለማድረግ ፅንፈኛው ተቃዋሚ እየጣረ ያለበት ሁኔታም ቢሆን ይታወቃል፡፡ በዚሁ ዓመት የግብፅ ኤምባሲ በርካሽ ዋጋ ለሥራ ወደ ግብፅ ለሚሄዱ ኢትዮጵያውያን በተለይ ወንዶች በሰጠው የገፍ ቪዛ እድል፤ እውነትም ሥራ ነው ብለው ወደዚያው የተጓዙ በርካታ ወጣቶች (በምስጢራዊ ድርድር) በማያውቁትና ባልፈለጉት መንገድ ሌሎችም አባላቶቻቸው በዚህ ሽፋን እንዲወጡ በሰጡት ምክር፤ ካይሮ ከደረሱ በኋላ ምን ችግር እንደገጠማቸው፤ መመለስ ቢፈልጉም እንዳልቻሉ፤ ግንቦት ሰባት ከካይሮ ተረክቦ ወደ ኤርትራ ለወታደራዊ ሥልጠና እንዳሸጋገራቸውም፤ ካይሮና አሥመራ ቢሮ ከፍቶ ከኦነግ፣ ከኦብነግ፣ ከሻዕቢያ እና አልሸባብ ኃይሎች ጋር ግንባት ሰባት ተባብሮ እንደሚሰራም ይታወቃል፡፡ ሻዕቢያ ለግንቦት ሰባት አመራርና አባላት መኖሪያ ቤት፤ ሙሉ ወጪ፤ ቢሮ፤ የራዲዮ ጣቢያና ወታደራዊ ማሰልጠኛ ጣቢያ እንደሰጠው፤ ሥልጠናው በሻዕቢያ መኮንኖች አማካይነት በባሬንቱ እንደሚሰጥ፤ የግንቦት ሰባት ሥራ አስፈፃሚም ቦታ ቀያይረው ሲሰበሰቡ፤ ቦታቸው፤ አጀንዳቸው፤ የሚያሳልፏቸው ውሣኔዎችም ይታወቃል፡፡

የግንቦት ሰባቱን የኢሣት ሣተላይት ራዲዮና ቲቪ ሥርጭት ዓመታዊ ወጪ በ97 ዓ.ም የአውሮፓ ሕብረት ልዑክ ኃላፊ ሆና ኢትዮጵያ የነበረችውና ከዶክተር ብርሀኑ ነጋ ጋር ቅርበት የፈጠረችው፤ የዶክተር ነገደ ጉበዜ ባለቤት ጎደኛ የሆነችው ሚስ

እና ጐሜዝ ከኒዩ ሊበራሉ ከበርቴ ጆርጅ ሶሮስ ተቋማት በምስጢር ጠይቃ ባገኘችው የሚሊዮኖች ዶላር በቋሚነት እንደሚረዳና ገንዘቡ ለሌላ ሥራም እንደሚውል ይታወቃል፡፡ በፖለቲካ ስትታመስና ስትመሰቃቀል፤ ሥርዓተ አልበኛነት ሰፍኖባት የቆየችው ሰፊ ግዛት ያላት የመን አልቃይዳና አልሸባብ በስፋት ይገኙባታል፡፡ የዚያኑ ያህልም በሕገ ወጥ ኮንትሮባንድ አማካይነት የሚሸጥ ከቀላል እስከ ከባድ የጦር መሣሪያ አለ፡፡ የግንቦት ሰባት ወኪሎች ሥውር ግዢ በማካሄድ ከየመን በጀልባ ወደ አሰብና ግመሎችን በመጠቀም ወደ አፋር ውስጥ ለማስገባት፤ ከአፋርም በመነሳት በግመል ወደተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በረሀ በረሀውን በመጠቀም ማድረስ ይቻላል ብለው ጥረት ማድረጋቸውም ቢሆን ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጽንፈኛና አክራሪ አሸባሪ የፖለቲካ ድርጅት ሙሉ እንቅስቃሴው በኢትዮጵያ፣ በአሜሪካን፣ በእንግሊዝ መንግሥትም ይታወቃል፡፡ ስለዚህም ምስጢራዊና ሕቡዕ ነኝ የሚለው ግንቦት ሰባት የሱ ምስጢራዊነት ካከተመ ገና ድሮ ቆይቷል፡፡ ኢሣት ባዶ ቀረርቶ እያሰማ ያፋዋጫል፤ ዶክተር ብርሀኑ ደግሞ እርምጃ እወስዳለሁ፤ እበቀላለሁ ሲል መግለጫ ያወጣል፤ ያስቃል፣ ያስገርማልም፡፡ ይኼኔ ነው የኮሜዲያን መስከረም "ጉዱ…ጉዴ" የሚለውን የክራር ዘፈን ዶክተር ብርሃኑና መሰሎቹ ሊጋበዙ የሚገባው፡፡